**181st Semiannual General Conference**
**Sunday Afternoon Session, October 2, 2011**

ሚስዮኖች የቤተክርስቲያኗ ሀብቶች ናቸው

በሽማግሌ ካዙኪ ያማሺታ

የሰባው አባል

ከብዙ አመት በፊት፣ አዲሱ ሚስዮን ሽማግሌ ስዋን እና የጃፓን አብሮ ተጓዢው በታችንን ለመጎብኘት መጡ። በቤት ስለነበርኩኝ፣ እንዲገቡ ለመጋበዝ ችለን ነበር። በበሩ ላይ ሰላም ስላቸው፣ አይኖቼ ሽማግሌ ስዋን ወደሚለብሰው ልብስ ተስበው ነበር። ሳላስብ፣ "የምትለብሰው ቆንጆ ኮት ነው" አልኩት። አዲስ ኮት አልነበረም እናም ቀለሙም እየጠፋ ነበር። ሽማግሌ ስዋን ከዚህ በፊት የነበረ ሚስዮን ትቶት የሄደውን ኮት እየለበሰ ያለ መስሎኝ ንበር።

ነገር ግን ሽማግሌ ስዋን መልስ ሰጠኝ እናም መልሱም ካሰብኩት በሙሉ የተለየ ነበር። ጥሩ ባልሆነ የጃፓን ቋንቋ እንዲህ መለሰ፥ "አዎን ይህ ጥሩ ኮት ነው። አባቴ በጃፓን ከ20 አመት በፊት እንደ ሚስዮን ሲያገለግል የለበሰው ኮት ነበር።"

አባቱ በጃፓን ኦከናዋ ሚስዮን አገልግሎ ነበር። ልጁ ወደ ጃፓን በሚስዮን ለማገልገል ሲሄድ፣ ኮቱን ሰጥቶት ነበር። ይህ ፎቶ ለሁለት ትውልድ ይለበስ የነበረ የሽማግሌ ስዋን ኮትን ያሳያል።

የሽማግሌ ስዋን ቃላትን ስሰማ ልቤ ተነካ። ወንጌልን ሲሰብክ ለምን የአባቱን ኮት እንደለበሰ ገባኝ። ሽማግሌ ስዋን ወደ ሚስዮኑ የሄደው የአባቱን ቅራጥነትና ለጃፓንና ለህዝቧ ያለውን ፍቅር በመውረስ ነበር።

እናንተ ወይም የምታውቋቸው እንደዚህ አይነት ነገር አጋጥሟችሁ ይሆን እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። በጃፓን የሚያገለግሉ የወንጌል መልእክተኞች አባታቸው፣ እናታቸው፣ አያታቸው፣ ወይም አጎታቸው በጃፓን እንዳገለገሉ ይነግሩኝ ነበር።

በአለም የተለያዩ ቦታዎች ላገለገሉት የወንጌል መልእክተኞች ያለኝን ልባዊ ፍቅር፣ ክብር፣ እና የምስጋና ስሜታ ለመግለፅ እፈልጋለሁ። ቀየራችኋቸው ፊታችሁን ወይም ስማችሁን እንዳልረሱ እርግጠኛ ነኝ። " "መልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፥ እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው።"

እኔም ከተቀየሩት አንዱ ነኝ። የተጠመቅኩት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤ ተማሪ እያለሁ በ17 አመቴ ነበር። የወንጌል መልእክተኛም ከአይደሆ የመታ ሽማግሌ ሩፐ ነበር። አሁን በአይደሆ እንደ ስቴክ ፕሬዘደንት እያገለገለ ነው። ከተጠመቅኩኝ በኋላ አላየሁትም ነበር፣ ነገር ግን በደብዳቤ እና በስልክ ላነጋግረው ችያለሁ። ደህና እንደሆንኩኝ ሲያውቅ በጣም ደስተኛ ነበረ። በምንም አልረሳሁትም። ጀኑ እና ፈገግተኛው ፊቱ በአዕምሮዬ ተቀርጿል። ደህና እንደሆንኩኝ ባወቀ ጊዜ ተደስቶ ነበር።

በ17 አመቴ፣ የለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ ነበር የተጠመቅኩት፣ ነገር ግን የወንጌል መልእክተኞቹ ያስተማሩኝ መልእክት በደንብ አልገባኝም ነበር። ነገር ግን ስለእነርሱ ልዩ ስሜታ ነበረኝ። እንደ ነርሱ ለመሆን ፈለግኩኝ። እናም ጥልቅ እና የሚጸና ፍቅራቸውም ተሰማኝ።

ስለተጠመቅኩበት ቀን ልንገራችሁ። በጣም በሚሞቅ በሐምሌ 15 ቀን ነበር። ሴት ተቀያሪም ከእኔ ጋር ተጠምቃ ነበር። የመጠመቂያው ገንዳ በወንጌል መልእክተኞቹ በእጅ የተሰራ ነበር፣ እናም ቆንጆም አልነበረም።

እንደተጠመቅን፣ ተረጋገጥን። መጀምሪያ እህቷ በሽማግሌ ሎይድ ተረጋገጠች። ከሌሎቹ የቤተክርስቲያን አባላት ጋር ተቀምጬ፣ አይኖቼን ጨፍኜ፣ እና በጸጥታ ቃላቱን ሰማሁ። ሽማግሌ ሎይድ አረጋገጣት፣ ከእዚያም በረከት ይሰጣት ጀመረ። ነገር ግን፣ ሽማግሌ ሎይድ መናገርን አቆመ፣ ስለዚህ አይኔን ከፈትኩኝና ፊቱን በቅርብ ተመለከትኩኝ።

በየቀኑም ይህን እይታ በግልፅ አስታውሳለሁ። የሽማግሌ ሎይድ አይኖች በእምባ ተሞልተው ነበር። በዚህም ጊዜ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እቅፍ ውስጥ እንዳለሁ ስሜታ የተሰማኝ። እናም በመንፈስ ቅዱስ በኩልሽማግሌ ሎይድ እንደሚያፈቅረን እና እግዚአብሔርም እንደሚያፈቅረን እርግጠኛ እውቀት አገኘሁ።

እህቷ ከተረጋገጠች በኋላ፣ የእኔ ተራ ነበር። እንደገናም ሽማግሌ ሎይድ ነበር የሚያረጋግጠኝ። እጁን በራሴ ላይ ጫነ እናም እንደ ቤተክርስቲያኗ አባል አረጋገጠኝ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ሰጠኝ፣ እናም በረከቶችን ሊሰጠኝ ጀመረ። እንደገናም መናገርን አቆመ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ከራሴ በላይ ምን እንዳለ አውቅ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ በኩል በእውነት የወንጌል መልእክተኞቹ እንደሚያፈቅሩኝ እና እግዚአብሔርም እንደሚያፈቅረኝ አወቅኩኝ።

በአለም ሁሉ ለሚያገለግሉት የወንጌል መልእክተኞች ሁሉ አንዳንድ ቃላት ልናገር እፈልጋለሁ። የምታሳዩት ጸባያችሁ፣ እናም ከሁሉም በላይ ወደ ሌሎች የምታሳዩት ፍቅር እራሳቸው ታላቅ መልእክቶች ናቸው። በአጋጠሙኝ ነገሮች መሰረት፣ የወንጌል መልእክተኞቹ ያስተማሩኝን በሙሉ እንዲገባኝ ባልችልም፣ እነርሱ ያሳዩኝ ፍቅርና ስራቸው ለእኔ በጣም አስፈላጊው መልእክት ሆነልኝ። እራሳችሁ በጣማስፈላጊ መልእክት ትሆናላችሁ። ይህም መልእክት የፍቅር መልእክት፣ የተስፋ መልእክት፣ እና የእምነት መልእክት ነው። በስራችሁም በአካባቢያችሁ ለሚገኙት ትሁትነትን፣ የዋህነትን፣ ልጋስን፣ እና ትዕግስትን እያስተማራችሁ ናችሁ። አስተሳሰባችሁ እና ስራችሁ መንፈስን ይጋብዛል፣ እናም አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች እንዲገባን የሚያደርገውም መንፈስ ነው። ከማንኛውም በላይ ልነግራችሁ የምፈልገው ነገር ቢኖር በፍቅራችሁ የእግዚአብሔርን ፍቅር እየተካፈላችሁ ናችሁ የሚለውን ነው። እናንተ መልእክት ናችሁ። የቤተክርስቲያኑ ሀብት ናችሁ። ለመስዋዕታችሁ፣ ለልብ ውሳኔአችሁ፣ በተግባር ላዋላችሁት፣ እና ቆራጥነታችሁ ለሁላችሁም ምስጋና አለኝ።

ለወደፊት ሚስዮኖች ልናገር እፈልጋለሁ። በቤተሰቤ አራት ልጆቻችን ሚስዮናቸውን ፈጽመዋል፣ እናም በዚህ ወር መጨረሻ ላይ አምስተኛው የወንጌል መልእክተኞችን ወደ ፕሮቮ የወንጌል መልእክተኛ ማሰልጠኛ ቦታ በዚህ ወር መጨረሻ ላይ ይገባል። በሚቀጥለው አመትም የመጨረሻው ልጃችንም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትን ከጨረሰ በኋላ በሚስዮን ለማገልገል አላማ አለው።

ስለዚህ በሚስዮን ለማገልገል ለምትዘጋጁት እናገራለሁ። ወደ ሚስዮን ስትሄዱ ሶስት ነገሮች ማምጣታችሁ አስፈላጊ ናቸው።

1. ወንጌልን ለመስበክ ያለ ፍላጎት። ጌታ በጎቹን እንድትፈልጉነ እንድታገኟቸው ይፈልጋል። በአለም ያሉ ብዙ ሰዎች እየጠበቋችሁ ናቸው። ወደአሉበት ቶሎ ሂዱ። ሌሎችን ለማዳን ከወንጌል መልእክተኞች በላይ በጣም የሚጥር የለም። ከተዳኑት አንዱም እኔ ነኝ።

“2. በምስክር ይኑራችሁ። ጌታ “ልባችሁን እና ፈቃደኛ የሆነ አዕምሮአችሁን” ይፈልጋል።

“3. ሌሎችን አፍቅሩ። የአባቱን ኮት እና ለጃፓን እና ህዝቦቿ የአባቱን ፍቅር እንዳመጣው እንደ ሽማግሌ ስዋን ሁኑ።

በሚስዮን ለማገልገል እንዴት እንደምትዘጋጁ ለማታውቁትም፣ ኤጲስ ቆጶሳችሁን ለማየት ባካችሁ ሂዱ። እንደሚረዳችሁ አውቃለሁ።

የወንጌል መልእክተኞችበጌታ በመጠራታቸው፣ ለጥሪውም መልስ በመስጠታቸው፣ እናም በአለም ሁሉ በማገልገላቸው ምስጋና ይሰማኛል። ከሚስዮን እተመለሳችሁትም እንዲህ ልበላችሁ---ለጥረታችሁ ሁሉ ምስጋና አለኝ። እናንተ የቤተክርስቲያኗ ሀብቶች ናችሁ። ወንጌል መልእክተኞችና እንደ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የምትሰሩ ሁልጊዜም ሁኑ።

የሰማይ አባታችን ልጆች እንደሆንን፣ እንደሚወደን፣ እናም ውድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እኛ ወደ እርሱ ፊት እንድንመለስ ዘንድ እንደላከው እመሰክራለሁ። እነዚህን ነገሮች የምለው በቅዱሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።